Amharic

# እችላለሁ ወይንስ አልችልም ?

ለእሳትሪፖርትለማድረግ

**000 መደወል**

በህዳር/November 2016 ዓ.ም ወቅታዊ የሆነ

ይህ መመሪያ ለእሳት አደጋ ጊዜያትና ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት በይፋ በሚታወጅበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚችሉና እንደማይችሉ አጠቃላይ የሆነ መረጃ ይሰጥዎታል፡ ታዲያ በክፍት ቦታዎች ላይ እሳት ለማንደድ በህግ የታገደ በሚሆንበትም ግዜ ነው።

የእሳት አደጋ ችግር ስለመጨመሩ CFA የእሳት አደጋ ጊዜያትን በቪክቶሪያ አስተዳደር በገጠር አካባቢ ባሉ ማዘጋጃ ቤቶች በኩል በይፋ ያውጃል። ስለርስዎ አካባቢ በበለጠ ዝርዝር መረጃ ለማየት በ CFA ድረገጽ፡ cfa.vic.gov.au ላይ ገብቶ ማየት። በመንግሥት ጫካዎች፤ ብሄራዊ ፓርክ/መናፈሻ እና በተከለለ ህዝባዊ መሬት ላይ ዓመቱን በሙሉ እሳት ማንደድ በህግ የተከለከለ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ስለ እሳት መከልከል ምክር ለማግኘት የአካባቢ፤ መሬት፣ ውሃ እና እቅድ አወጣጥ መምሪያን (DELWP) ማነጋገር። እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ዓመቱን በሙሉ ስለሚከለከል ሁልጊዜ ከርስዎ ማዘጋጃ ቤት ያለውን ሁኔታ ማጣራት ነው።

እሳት በፍጥነት እየተሰራጨ ሲመጣና ለመቆጣጠር አስቸጋሪ በሚሆንበት ቀናት፤ ጠቅላላ የእሳት እገዳዎች በ CFA በኩል በይፋ ይታወጃል። በእሳት አደጋ ጊዜ እና ጠቅላላ በእሳት እገዳ ቀናት ላይ እሳት ማንደድ ህገ-ወጥ እንደሆነና ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣትና ወደ እስርቤት መግባትንም ያጠቃልላል።

## ስጋ መጥበሻ/ barbecue፤ ማድረግ የካምፕ እሳት ማንደድ ወይም ለሙቀት ወይም ለምቾት በሚል እሳት ማንደድ እችላለሁን?





## በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- ነፋሱ በሰዓት ከ10 ኪሎ ሜትር በላይ ካልሆነ (ይህን ማወቅ የሚቻለው ቅጠሎችና ትናንሽ ቅርንጫፎች ያለማቋረጥ ሲወዛወዙ ነው)
- **በተገቢው የታነጸ የእሳት ቦታ** ላይ ወይም ቢያንስ 30 ሴንቲ ሜትር ጥልቀት ባለው በቦይ ውስጥ እሳት ሲቀጣጠል
- ከእሳቱ ክልል ዙሪያ ውጭ በ3 ሜትሮች እርቀት ውስጥ ያለ አካባቢ እና በላይኛው የእሳት ገጽታ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ የሆነ
- እሳቱ ከ 1 ሜትር ስኩዌር ስፋት በላይ ቦታ መያዝ እንደሌለበት እና የሚጠቀሙት ጥሬ ማቀጣጠያ መጠኑና ስፋቱ ለተፈለገው ዓላማ በአነስተኛ ማድረግ
- እሳቱ በሚነድበት ጊዜ እሳቱን ለማጥፋት የሚችል እና አቅም ያለው ሰው ሁልግዜ መገኘት አለበት።
- ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉበሙሉ መጥፋት አለበት፡

*ማሳሰቢያ፡ የ CFA አንቀጽ ህግ/Act 1958 ዓ.ም እንደሚገልጸው፤* በተገቢው ለታነጸ እሳት ማንደጃ ቦታ፤ ይህም ከድንጋይ፤ ብረት፤ አሸዋና ስሚንቶ ወይም ከሌላ ከማይቀጣጠል ቆሳቁስ የተሰራ እንደሆነና በእሳቱ ያለን ዙሪያ ያካተተ ነው። ለንግድ ተብሎ የተመረተ ስጋ መጥበሻ ባርባኪው በተገቢው የታነጸ የእሳት ማንደጃ ቦታ ስለመሆኑ ግምት ውስጥ ማስገባት ነው።

## ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**የካምፕ እሳት፤ ለማሞቂያ ወይም ለግለሰብ ምቾት እሳት በሙሉ በጠቅላላ እሳት እገዳ ቀናት ጊዜ የታገደ ነው። እንዲሁም በጥሬና ፈሳሽ ማቀጣጠያ የስጋ መጥበሻ ባርቢኪው እና ምድጃዎች (ሃንጊስ/hangis ያካተተ) በጠቅላላ የእሳት እገዳ በተደረገበት ቀናት የተከለከለ ነው።**

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- ስጋ መጥበሻ ባርቢኪው የሚጠቀመው በጋዝ ወይም ኤሌትሪክ እንደሆነና በቋሚነት የተገጠመ ሲሆን ይህም ከድንጋይ፤ ብረት፤ አሸዋና ስሚንቶ ወይም ከሌላ ከማይቀጣጠል ቆሳቁስ የተሰራና ለምግብ ማዘጋጃ ተብሎ በተለይ የታቀደ እና ለንግድ ሥራ ተብሎ የተመረተ ምግብ ማዘጋጃ (ተንቀሳቃሽ ባርቢኪዮችን ያካተተ) እንደሆነና እሳት በሚቃጠልበት ጊዜ በአንድ ቋሚ ቦታ ከተቀመጠ
- ከስጋ መጥበሻ ባርቢኪው ክልል ዙሪያ ውጭ በ3 ሜትሮች እርቀት ውስጥ ያለ አካባቢ ከሚቀጣጠል ነገሮች ነጻ የሆነ
- ወዲያውኑ ስራ ላይ የሚውል ከውሃ አቅርቦት ጋር የተቀጠለ ቱቦ ወይም ከ10 ሊትር ያላነሰ ውሃ የሚይዝ ማጠራቀሚያ ሊኖርዎት ይገባል፡
- እሳት በሚቃጠልበት ጊዜ እሳትን ለማጥፋት አቅምና ዘዴ ያለው አንድ ጎልማሳ በቦታው ላይ ሁልጊዜ ይኖራል
- ይህ ጎልማሳ ሰው ከአካባቢው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉበሙሉ መጥፋት አለበት፡

## የምግብ ዝግጅት የንግድ ሥራ አካሂዳለሁ (ለምሳሌ፡ ለድግስ ምግብና መጠጥ ማቅረብ) ወይም እኔ በማህበረሰብ/በበጎ አድራጊ/በገንዘብ እርዳታ ማሰባሰብ ወይም በተመሳሳይ ድርጅት ውስጥ እሰራለሁ። ከቤት ውጭ በሚካሄድ ድርጊት ላይ የስጋ መጥበሻ/ባርባኪው፤ ማብሰያ ወይም የምግብ ማሞቂያ እንዲሰራ በማቀናጀት እሳትን መለኮስ እችላለሁን?



## በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- ነፋሱ በሰዓት ከ10 ኪሎ ሜትር ፍጥነት በላይ ካልሆነ (ይህን ማወቅ የሚቻለው ቅጠሎችና ትናንሽ ቅርንጫፎች ያለማቋረጥ ሲወዛወዙ ነው)
- **በተገቢው የታነጸ የእሳት ቦታ** ላይ ወይም ቢያንስ 30 ሴንቲ ሜትር ጥልቀት ባለው በቦይ ውስጥ እሳት ከተለኮሰ
- ከእሳት ደንበር ዙሪያ ውጭ በ3 ሜትሮች እርቀት ውስጥ ያለ አካባቢ እና በላይኛው የእሳት ገጽታ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ ሲሆን
- እሳቱ ከ 1 ሜትር ስኩዌር ስፋት በላይ ቦታ መያዝ እንደሌለበት እና የሚጠቀሙት ጥሬ ማቀጣጠያ መጠኑና ስፋቱ ለተፈለገው ዓላማ በአነስተኛ ማድረግ
- እሳቱ በሚነድበት ጊዜ እሳቱን ለማጥፋት የሚችል እና አቅም ያለው ሰው ሁልግዜ መገኘት አለበት።
- ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉበሙሉ መጥፋት አለበት፡

እነዚህ ሁኔታዎች ለማሟላት ካልቻሉ ከ CFA ወረዳ ቢሮ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይኖርብዎታል።

## ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**አይቻልም፡ ጽሁፋዊ ፈቃድ በ CFA, MFB ወይም DELWP ካልተሰጠ በስተቀር በዚያ ፈቃድ ላይ ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ይከተላሉ።**

የማህበረሰብ ድርጅት፤ የበጎ አድራጊ ድርጅት ወይም በገንዘብ እርዳታ አሰባሰብ ተሳትፎ ያለው ድርጅት (ለምሳሌ፡ የትምህርት ቤት ወይም የስፖርት ቡድን) ሥራቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ምግብ ለማዘጋጀት ለማዘጋጀት የእሳት ማንደድ ፍቃድ ሊያመለክቱ ይችላሉ። እሳት በተከለከለበት አካባቢዎች ውስጥ እነዚህ ፈቃዶች የሚሰጡት በአካባቢ CFA የወረዳ ቢሮዎች፤ በCFA ጠቅላይ መምሪያ ቢሮዎች፤ የMFB የወረዳ ቢሮዎች ወይም በDELWP እሳት ዋና ሀላፊ በኩል ይሆናል።

የማዘጋጃ ቤት እሳት መከላከያ ሀላፊዎች እነዚህን ፈቃዶች መስጠት አይችሉም።

# እችላለሁ ወይንስ አልችልም ?

ስለ እሳት ለማሳወቅ ለማመልከት
**000 መደወል**

## ለስጋ መጥበሻ የሚያገለግል መጥበሻ (rotisserie) ላይ በከሰል ፤እንጨት ወይም ሌላ ጥሬ የሚቃጠል መጠቀም እችላለሁን?



### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- ነፋሱ በሰዓት ከ10 ኪሎ ሜትር በላይ ካልሆነ (ይህን ማወቅ የሚቻለው ቅጠሎችና ትናንሽ ቅርንጫፎች ያለማቋረጥ ሲወዛወዙ ነው)
- **በተገቢው የታነጸ የእሳት ቦታ** ላይ ወይም ቢያንስ 30 ሴንቲ ሜትር ጥልቀት ባለው ቦይ ውስጥ እሳት ሲቀጣጠል
- ከእሳት ክልል ዙሪያ ውጭ በ3 ሜትሮች እርቀት ውስጥ ያለ አካባቢ እና በላይኛው የእሳት ገጽታ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ ሲሆን
- እሳቱ በሚነድበት ጊዜ እሳቱን ለማጥፋት የሚችል እና አቅም ያለው ሰው ሁልግዜ መገኘት አለበት።
- እሳቱ በሚነድበት ሁልጊዜ አንድ ሰው በተገኘበት ሲሆን ታዲያ እሳቱን ማጥፋት አቅምና መፍትሄ ይኖረዋል።
- ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋት አለበት፡

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**የለም**

**በጥሬ ማቀጣጠያ ባርቢኪዎች መጠቀም በተከለከለ ክፍት ቦታ ላይ እና ጠቅላላ የእሳት እገዳ ቀናት ላይ አይፈቀድም።**

*ያስተውሉ፡ የ CFA አንቀጽ ህግ/Act 1958 ዓ.ም እንደሚገልጸው፤* በተገቢው ሊታነጸ እሳት ማንደጃ ቦታ፤ ይህም ከድንጋይ፤ ብረት፤ አሸዋና ስሚንቶ ወይም ከሌላ ከማይቀጣጠል ቆሳቁስ የተሰራ እንደሆነና የእሳቱን ዙሪያ ያካተተ ነው። ለንግድ ተብሎ የተመረተ ባርቢኪው በተገቢው የታነጸ የእሳት ማንደጃ ቦታ ስለመሆኑ ግምት ውስጥ ማስገባት።

## በጋዝ-ለሚቀጣጠል የዱር አራዊት ማስፈራሪያ ጠበንጃ መጠቀም እችላለሁን?



### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- የአሁን ጊዜ Schedule 14 ፈቃድ (የእሳት ማንደድ ፍቃድ) ካለዎት እያንዳንዱን እና ሁሉንም ሁኔታዎች ይከተሉ

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**አይቻልም**

በጋዝ-ሃይል የሚሰራ ማስፈራሪያ ጠበንጃዎች ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት መጠቀም አይቻልም።

## በክፍት ቦታ ላይ ሳር፤ እብቅ፤ አረም፤ ቁጥቋጦችን ወይም አትክልቶችን በእሳት ማቃጠል እችላለሁን?



### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- በማዘጋጃ ቤት የእሳት መከላከያ ሀላፊ ወይም በCFA ወረዳ ቢሮ በኩል የተሰጠ ጽሁፋዊ ፈቃድ ካለዎት
- ከመንግስት ተወካይ የእሳት መከላከያ ሀላፊ በኩል የተሰጠ ጽሁፋዊ ፈቃድ ካለዎት
- በዚያ ፈቃድ ያሉትን ሁኔታዎች ከተከታተሉ
- እሳቱ በሚነድበት ጊዜ እሳቱን ለማጥፋት የሚችል እና አቅም ያለው ሰው ሁልግዜ መገኘት አለበት።
- ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋት አለበት፡

ብዙዎች ምክር ቤቶች የራሳቸው ህጎች እንዳሏቸው፤ ይህም በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ወይም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ወይም በተወሰኑ ጊዜያት በእነሱ ማዘጋጃ ቤቶች ውስጥ እሳት ማቀጣጠል ክልክል እንደሆነ ነው። ያለውን ሁኔታ ከማዘጋጃ ቤት የእሳት መከላከያ ሀላፊ ማጣራት ነው።

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**አይፈቀድም**

ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት ውስጥ በክፍት ቦታ ላይ ሳርን፤ እብቅ ችፍርግ ወይም ቆሻሻን ማንደድ የተከለከለ ነው።

በማዘጋጃ ቤት የእሳት መከላከያ ሀላፊዎች የተሰጡት ፈቃዶች በሙሉ ለጠቅላላ እሳት እገዳ ቀን የታገዱ ናቸው።

አሁን ያለው ማንኛውም እሳት፤ ማለት በእሳት አደጋ ጊዜ በማይመለከተው ወይም ፈቃድ ባለው መሰረት ማካሄድ ለሚችሉት አካትቶ የነበረን አጠቃላይ እሳት እገዳ ከመጀመሩ በፊት የማይፈቀድ እና እሳቱም ሙሉ በሙሉ መጥፋት አለበት።

## ተሽከርካሪው ከሰብል፤ ሳር፤ እብቅ፤ አረም፤ ቁጥቋጦች ወይም ከአትክልቶች ጋር ግንኙነት ባለበት ቦታዎች ላይ ተሽከርካሪ መንዳት እችላለሁን?

### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- በተሽከርካሪው ላይ ብቃት ያለው የማስወገጃ መሳሪያ (ለምሳሌ፡ ጭስ ማውጫ/muffler) ከተገጠመለት፤ ይህም ከሞተሩ የሚወጣውን ጭስ በሙሉ ይወስድና በማስወገጃ መሳሪያው ውስጥ ያሳልፈዋል።

ጠቅላላ የእሳት እገዳ ቀን ባይኖርም ከተሽከርካሪው በሚወጣው ሙቀት ችግር ሊፈጥር ስለሚችል፤በሞቃትና ደረቅ ባለበት ሁኔታ ላይ እና የደረቁ አትክልቶች ባሉበት ቦታ ላይ ተሽከርካሪ መንዳት የለብዎትም።

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- በተሽከርካሪው ላይ ብቃት ያለው የማስወገጃ መሳሪያ (ለምሳሌ፡ ጭስ ማውጫ/muffler) ከተገጠመለት፤ ይህም ከሞተሩ የሚወጣውን ጭስ በሙሉ ይወስድና በማስወገጃ መሳሪያው ውስጥ ያሳልፈዋል።

የትም ይሁን ይህ በተቻለ መጠን መወገድ አለበት፤ ምክንያቱም ለእሳት መነሳት ከፍተኛ እንደሆነና በነዚህ ቀናት ውስጥ የሚከሰተው ችግር ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ነው።

# እችላለሁ ወይንስ አልችልም ?

ለእሳትሪፖርትለማድረግ
**000 መደወል**

## መጋዝ፤ የእጸዋት ወይም የሳር መቁረጫ ወይም ሳር ማጨጃ መሳሪያ መጠቀም እችላለሁን?





### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- አረንጓዴ ላልሆነ አትክልት (ይህም ደረቅ ለሆነ አትክልት) መጋዝ፤ የአትክልት ወይም ሳር መቁረጫ ወይም ሳር ማጨጃ መሳሪያ ሲጠቀሙ ከዚህ በታች ያሉትን ሁኔታዎች መከተል:
  - እሳት ሊፈጥር ከሚችል ብልሽትና የመካኒካል ጉድለት ነጻ መሆን
  - ብቃት ካለው ለእሳት ፍንጣሪ ማስወገጃ መግጠም
  - ከመሳሪያው ቢያንስ በ 3 ሜትሮች ዙሪያ ላይ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ ማድረግ ነው።

እንዲሁም መሳሪያው በሚሰራበት ማንኛውም ጊዜ አንድ ሰው መገኘት እንዳለበትና ከዚህ በሚከተሉት የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ እቃዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን መያዝ አለበት:

- ሙሉ በሙሉ የሚሰራና በውሃ የተሞላ ቢያንስ አንድ የመርጫ መንፊያ ከ 9 ሊትር በታች ያልሆነ ውሃ መያዝ የሚችል፤ ወይም
- ቢያንስ አንድ የውሃ (ለተጠራቀመ ግፊት) እሳት ማጥፊያ/fire extinguisher፤ የሚሰራና በውሃ የተሞላ ትክክለኛ ግፊት ያለው እና ከ 9 ሊትር በታች ያልሆነ ውሃ መያዝ የሚችል ይሆናል።

በአረንጓዴ አትክልት ባለው ፈቃድ መሰረት መሥራት፤ ይሁን እንጂ መሳሪያውን መጠበቅ እና የእሳት ማጥፊያ መሳሪያውን ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መከናወን እንዳለበት በCFA ሃሳብ ቀርቧል።

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

በጠቅላላ እሳት እገዳ ቀናት የትም ይሁን ይህ በተቻለ መጠን መወገድ አለበት፤ ምክንያቱም እሳትን መለኮስ በጣም አደገኛ እና በአሁኑ ግዜ በእሳት አደጋ ምክንያት የሚከሰተው ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ነው።

ሥራው አስፈላጊ ከሆነ በእሳት አደጋ ጊዜ አጠገብ ባለው ክፍል ያሉትን መመሪያዎች መከተል።

ማሳሰቢያ፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የእሳት ፍንጣሪ ርጭት መከላከያ፤ የውሃ መርጫ ማጠራቀሚያ እና የውሃ እሳት ማጥፊያ በአውስትራሊያ ጥራት ደረጃ መሰረት ያሟሉ መሆን አለባቸው።

## ማካሄድ እችላለሁን:

- **የብረት ማቅለጥ፤ የመፍጨት፤ የማቃጠል፣ የብየዳ ወይም ጋዝ የማቋረጥ ሥራ?**
- **የባቡር ሃዲድ ጥገና?**
- **ቅርጣንን የማሞቅ?**
- **የንብ ጭስ በመጠቀም ንቦችን የማስለቀቅ?**
- **ሙቀት ወይም በእሳት ነበልባልን በመጠቀም ማር የማውጣት?**



### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- የእሳት ፍንጣሪዎችን፤ ከሞቀ ብረትን ወይም ከእሳት የሚጣለውን ለማቆም እሳት-ለማያሳልፍ ሽፋን ወይም ማገጃ በማስቀመጥ መከላከል
- ሥራው ከሚካሄድበት ቢያንስ 1.5 ሜትር ያለው እርቀት አካባቢ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ መሆን ወይም እሳቱ እንዳይዛመት በበቂ እርጥበት መከላከል
- የውሃ አቅርቦት ባለው ወይም ቢያንስ 9 ሊትር ውሃ ከያዘ የውሃ መርጫ ማጠራቀሚያ ጋር የተቀጠለ ውሃ ቱቦ ካለዎት
- ከሥራ ላይ የተቆራረጡ እና ሞቃታማ ነገሮች ሁሉ እሳት-በማይገባበት ማጠራቀሚያ ውስጥ ይቀመጣሉ
- እሳቱ በሚነድበት ሁልጊዜ እሳቱን የማጥፋት አቅምና መፍትሄ ያለው አንድ ሰው መገኘት አለበት፡
- ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋት አለበት

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**የለም**

**እነዚህ ሥራዎች በአጠቃላይ የእሳት እገዳ ቀናት ላይ የተከለከሉ ናቸው።**

በእሳት እገዳ ቀናት ላይ መጠነኛ በሆኑ ሁኔታዎች፤ የCFA፤ MFB ወይም DELWP ክፍል 40 ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

እነዚህ ፈቃዶች የሚሰጡት በCFA የወረዳ ቢሮዎች፤ በCFA ዋና የመምሪያ ቢሮዎች፤ በMFB ወረዳ ወይም በDELWP ቢሮዎች በኩል ነው። በማዘጋጃ ቤት የእሳት መከላከያ ሃላፊዎች በኩል መሰጠት እንደማይችል ነው።

ለክፍል 40 ፈቃድ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ በዚህ ገጽ ጀርባ ያለውን ዝርዝር መረጃ ማየት።

# እችላለሁ ወይንስ አልችልም ?

ለእሳትሪፖርትለማድረግ
**000 መደወል**

## ቆሻሻ ማቃጠያ በርሜልን መጠቀም እችላለሁን?

### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

1. በቆሻሻ መጣያ አጠቃቀም ያለውን ማስጠንቀቂያ ወይም እገዳ ሊገልጽ ስለሚችል ማንኛውም የአካባቢ ህጎች በምክር ቤት በኩል ያጣሩ (ለምሳሌ፡ በአንዳንድ ቀናት፤ በአንዳንድ አካካቢዎች ወይም በአንዳንድ ጊዜያት ያለን የእገዳ ትእዛዝ)
2. እንዲሁም የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት:
   - እሳቱ ከቆሻሻ ማቃጠያ በርሜል ውስጥ መውጣት የለበትም፡
   - ነፋሱ በሰዓት ከ10 ኪሎ ሜትር ፍጥነት በላይ ካልሆነ (ይህን ማወቅ የሚቻለው ቅጠሎችና ትናንሽ ቅርንጫፎች ያለማቋረጥ ሲወዛወዙ ነው)
   - በመሬት እና በአየር ላይ ያለው ክፍት ቦታ ከቆሻሻ ማቃጠያ በርሜል ዙሪያ ውጭ በ3 ሜትሮች እርቀት ውስጥ ያለው አካባቢ ከሚቀጣጠል ነገር ነጻ ሲሆን
   - እሳት በሚቀጣጠልበት ጊዜ እሳቱን ለማጥፋት የሚያስችል በቂ የውሃ አቅርቦት መኖር አለበት
   - እሳቱ በሚነድበት ሁልጊዜ እሳቱን የማጥፋት አቅምና መፍትሄ ያለው አንድ ሰው መገኘት አለበት።
   - ሰውየው ከቦታው ከመሄዱ በፊት እሳቱ ሙሉ በሙሉ መጥፋት አለበት፡

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

**አይቻልም**

የቆሻሻ ማቃጠያ በርሜል መጠቀም እሳት እገዳ ቀናት ላይ የተከለከለ ነው።

ማሳሰቢያ፡ *የCFA አንቀጽ ህግ/Act 1958* ዓ.ም እንደሚገልጸው፤ቆሻሻ ማቃጠያ በርሜል የተሰራው ወይም የታቀደው ላልተፈለጉ ነገሮች በማቃጠል ለማስወገድ የሚጠቅም እንደሆነና:

- ከማይቀጣጠል ነገር የተሰራ እንደሆን፤ እና
- ከእሳት ፍንጣሪ፤ ከፉም ረመጥ ወይም ሌላ ከሚነድ ነገር  የሚወጣውን ነበልባል ለመከላከል በማይቀጣጠል ነገር የተሸፈነ ወይም መከላከያ ያለው ነው።

## በ 9 ሜትሮች መካከል ባለ ማንኛውም ሰብል፤ ሳር፤ እብቅ፤ አረም፤ ቁጥቋጦ ወይም ሌላ አትክልት ላይ በራሱ ለሚንቀሳቀስ የእርሻ መሳሪያ፤ መቆፈሪያ፤ ትራክተር፤ እንጨት መቁረጫ፡ የሚቆፍር መሳሪያ ወይም የመንገድ መሥሪያ መሳሪያዎች በሙቀት በሚሰራ ሞተር መጠቀም እችላለሁን?

### በእሳት አደጋ ጊዜ

**አይቻልም፤ ከዚህ የሚከተለው ካልሆነ በስተቀር:**

- እሳት ሊፈጥር ከሚችል ብልሽትና የመካኒካል ጉድለት ነጻ ከሆነ
- እንዲሰራ በሚያስችል በራሱ ተሽከርካሪ የሆነ ብቃት ያለው ለእሳት ፍንጣሪ ማስወገጃ የአየር ማጣሪያ የተገጠመለት
- የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ ስለሚሸከም ከሚከተሉት አንዱን ያካትታል:
  - ሙሉ በሙሉ የሚሰራና በውሃ የተሞላ ቢያንስ አንድ የመርጫ መንፊያ ከ 9 ሊትር በታች ያልሆነ ውሃ መያዝ የሚችል፤ ወይም
  - ቢያንስ አንድ የውሃ (ለተጠራቀመ ግፊት) እሳት ማጥፊያ/fire extinguisher፤ የሚሰራና በውሃ የተሞላና ትክክለኛ ግፊት ያለው እና ከ 9 ሊትር በታች ያልሆነ ውሃ መያዝ የሚችል ይሆናል።

### ጠቅላላ እሳት በተከለከለበት ቀናት

የትም ይሁን ይህ በተቻለ መጠን መወገድ አለበት፤ ምክንያቱም እሳትን መለኮስ በጣም አደገኛና በአሁኑ ግዜ በእሳት አደጋ ምክንያት የሚከሰተው ችግር ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ነው።

ሥራው አስፈላጊ ከሆነ በእሳት አደጋ ጊዜ አጠገብ ባለው ክፍል ያሉትን መመሪያዎች መከተል።

ማሳሰቢያ፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የእሳት ፍንጣሪ ርጭት መከላከያ፤ የውሃ መርጫ ማጠራቀሚያ እና የውሃ እሳት ማጥፊያ (water fire extinguisher) በአውስትራሊያ ጥራት ደረጃ መሰረት ያሟሉ መሆን አለባቸው።

---

በእሳት መጠቀም እገዳ ያሉትን ህጎች ስለመከተል ማረጋገጥ የእያንዳንዱ የእሳት ተጠቃሚ ሃላፊነት ይሆናል።

ማንኛውም የእሳት ተጠቃሚዎች በሚያካሂዱት ድርጊት እሳቱ ወደሌላ ንብረት እንዲሰራጭ ምክንያት ላለመሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው። *በወንጀል አንቀጽ ህግ/ Crimes Act 1958 (Vic)* መሰረት ሆነ ብሎ ወይም በግድየለሽነት እሳት መለኮስ፤ እሳትን ባለመቆጣጠር እና ወደሌላ ንብረት እንዲሰራጭ መፍቀድ ከባድ ቅጣቶችን ያስከትላል።

**በንብረቴ ላይ እሳት ለማንደድ አቅጀአለሁ። ለድንገተኛ ችግር ደራሽ አገልግሎቶች (emergency) እንዴት ማሳወቅ እችላለሁ?**

በCFA ወይም በማዘጋጃ ቤት እሳት መከላከያ ሀላፊ እሳት ለማንደድ  ፈቃድ ተሰጥትዎት ከሆነ፤ ይህንን ፈቃድ ለድንገተኛ ችግር ደራሽ አገልግሎቶች የቴሌኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን (ESTA) አስቀድመው በስልክ 1800 668 511 በመደወል ማሳወቅ አለብዎ፡ በተጨማሪም በፍቃዱ ካሉት ሁኔታዎች ውስጥ የተጠቀሰ ሰው ካለ ማሳወቅ።

**በበለጠ መረጃ ለማግኘት ወይም ለፈቃድ ማመልከት እንዴት እችላለሁ?**

ስለዚህ መመሪያ፤ ወይም የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ማንኛውንም መግለጫ ወይም በበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ፡ cfa.vic.gov.au ላይ ገብቶ ማየት፤
ለአካባቢዎ የCFA ወረዳ ዋና መምሪያ ቢሮ በአካል ወይም በስልክ (03) 9262 8444 ደውሎ ማነጋገር። ለCFA ወረዳ ዋና መምሪያ ቢሮዎች የስልክ ቁጥሮች ዝርዝር በ CFA ድረገጽ ላይ ቀርቧል።

በከተማ ክልል ባለ የእሳት ወረዳ ውስጥ ለመሥራት ፈቃድ ማግኘት ካስፈለግዎ፤ ለMFB በስልክ (03) 9662 2311 ደውሎ ማነጋገር ወይም በድረገጽ፡ mfb.vic.gov.au ላይ ገብቶ ማየት።

በሰሜን-ምስራቅ እና ምስራቃዊ ሜልበርን ባሉት ብዙዎች ማዘጋጃ ቤቶች ውስጥ በህዝባዊ መሬትና በድንበር መስመር ላይ የ1.5 ኪ.ሜ እርቀት የDELWP እሳት እገዳ ተግባራዊ ይሆናል። ዝርዝር መረጃ በDELWP ድረገጽ ላይ ማጣራት።

ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ካስፈለግዎ፤ ለDELWP በስልክ 136 186 ደውሎ ማነጋገር ወይም በድረገጽ፡ delwp.vic.gov.au ላይ ገብቶ ማየት።

mfb.vic.gov.au  cfa.vic.gov.au